## የሚረዱ፣ የተሌፎን ቁጥሮች።

እባክዎን፣ አጠገብዎ ወደሚገኘው የስደተኛ የጤና ግምገማ ወኪል በመደወል፣ ስለ ፕሮግራሙ ተጨማሪ ማብራርያ ይጠይቁ። የሚቀጥሉት የተሌፎን ቁጥሮች ብዙ ስደተኞች የሚኖሩባቸው ወረዳዎች (counties) የጤና አገልግሎት ናቸው።

| | |
|---|---|
| Anoka | 763-422-7030 |
| Carver | 952-361-1329 |
| Clay | 218-299-5220 |
| Dakota | 952-891-7500 |
| Hennepin | 612-348-7006 |
| Nobles-Rock | 507-295-5272 |
| Olmsted | 507-328-7500 |
| Otter Tail | 218-998-8320 |
| St. Paul-Ramsey | 651-266-1251 |
| Stearns | 320-203-6942 |
| Washington | 651-430-6655 |

የሚኖሩበት ወረዳ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከሌለ፣ ወኪልዎ'ጋ (VOLGA) ወይም የሚነሶታ የጤና አገልግሎት ፕሮግራም በ651-201-5414 ደውለው ይጠይቁ።

ይህ ፕሮግራም፣ በስደተኛ የጤና አገልግሎት፣ የሚነሶታ የጤና አገልግሎት ክፍል፣ ከማሳቹሰትስ (Massachusetts) የጤና አገልግሎት ያገኘው ነው

December 2009 IC# 141-1058 (Amharic)

**Minnesota Department of Health**
Refugee Health Program
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 554164-0975

# የስደተኛ ጤና ግምገማ።

ወደሚኖሶታ፣ እንኳን በደህና መጡ።



የሚነሶታ
የጤና ክፍል
የስደተኛ ጤና ፕሮግራም

## የስደተኛ የጤና ግምገማ ምንድነው ?

የስደተኛ የጤና ማጣርያ ፕሮግራም በተባበሩት የአመሪካ አገሮች (United States) የመጀመርያ የጤና አገልግሎት ነው። የሙሉአካል የጤና ምርመራ ሲሆን፥ ወደስራ ወይም ትምህርት ቤት ለመሄድ የሚከለክልዎት የበሽታ ችግር ካለ ለማወቅ ነው። የስደተኛ የበሽታ ግምገማ፥ በጣም አስፈላጊና እዚህ አገር ለመኖር አዲስ ህይወት የሚጀምሩበት ነው።

ስደተኞች በሙሉ፥ ጥገኛነት የጠየቁ፥ ጥገኝነት የተሰጣቸው፥ የኩባ ወይም የሃይቲ ተወላጆች ወደ ሚነሶታ ከገቡ የሚወስዱት ምርመራ ነው።

የጤናው ምርመራ ሁለት ጊዜ፥ ወደ ሃኪም ወይም ክሊኒክ በመሄድ ምርመራ ለማድረግ የሚረዳ ሲሆን፥ የሚከተሉት ምርመራዎች ያደርጋል።

- በውጭ አገር ያደረጉት የጤና ምርመራ ያያል
- የጤና ታሪክዎን ያያል
- የአካል ምርመራ ያደርጋል
- የበሽታ ምርመራ ያደርጋል
- የሚያስፈልግ ክትባት ይሰጣል

የጤና ምርመራው፥ ሚነሶታ ከገቡ በ90 ቀናት ውስጥ መደረግ አለበት። ምርመራ ሲያደርጉ አስተርጓሚ ይዘው ይሂዱ።

## ውጭ ካደረጉት ምርመራ፥ ልዩነቱ ምንድ ነው ?

ምርመራው፥ ወደ አመሪካ ለመግባት የሚያስከለክሉት በሽታዎች፥ እንደ ሳንባ በሽታ፥ የአካል ወይም የአእምሮ በሽታ፥ እንደ ንዴትና ዕጸፋርስ የመሳሰሉት ሱስነት ካለብዎት ለማወቅ ነው።

## ምን ያህል ገንዘብ ያስ ልጋል ?

ምርመራው ነፃ ነው። ክፍያው ከሚቀጥሉት ውስጥ በሁለት መንገድ ይከፈላል የህክምና እርዳታ ካርድ ካለዎት፥ የሚነሶታ የህክምና እርዳታ ይከፍለዋል። ካርድ ከሌልዎትና እዚህ አገር ከመጡ ከ90 ቀናት በታች ከሆነ፥ የሚነሶታ የህክምና ክፍል ለታከሙበት ክሊኒክ ይከፍላል።

## ምን ይዤ ልምጣ ?

የህክምና ምርመራ ሲያደርጉ፥ ካለዎት፣ የሚከተሉትን ይዘው ይምጡ።

- IOM ( International Organization for Migration) የክትባትና የህክምና ወረቀቶችን የያዘ ሻንጣ
- የክትባት ወረቀቶች
- ተጨማሪ የሕክምና ወረቀቶች
- የሚወስዱት መድሃኒት ካለ

## ቦታው የት ነው ?

የጤና ማጣርያ ምርመራ ሰ ርዎ ከሚገኘው የሕዝብ ህክምና አገልግሎት (Local Public Health Agency) ወይም የራስዎ ሕክምና ክሊኒክ ነው።

## ሎካል ፓብሊክ ሄልዝ ኤጀንሲ (LOCAL PUBLIC HEALTH AGENCY) ምንድነው ?

ሎካል ፓብሊክ ሄልዝ ኤጀንሲ፥ በሁሉ የሚነሶታ ወረዳዎች ይገኛል። ለአንድ ዓመት፥ የጤና ግምገማ ምርመራ ለማድረግ፥ ቀጠሮ በመውሰድ የሚረዳዎት ነው። ሌላ ተጨማሪ እርዳታዎችንም ያደርጋል። ለምሳሌ፣ ክትባት ይሰጣል፥ ይመረምራል፥ በሽታዎችንም ያክማል።

## ፕራይመሪ ኬር ፕሮቫይደር (PRIMARY CARE PROVIDER) ምንድነው ?

ፕራይመሪ ኬር ፕሮቫይደር ማለት፥ ሁሉጊዘ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥዎ ት ክሊኒክ ወይም ሃኪም ነው። በተለይ፣ ከታመሙ የሚያክም፥ ክትባትየ ሚሰጥ፥ ቀጣይ ማለት የረጅም ጊዜ ህክምና የሚሰጥና አስፈላጊ ከሆነም ወደሌላ ሃኪም የሚልክዎት ነው።

ፕራይመሪ ኬር፥ ብዙ የህክምና አገልግሎት ስላለው፥ የሚያስፈልግዎትን ህክምና ሊያገኙ ይችላሉ።